# ያንተ ሽበት



ለወለላዬ ከአክብሮት ጋር

ቢገረጣም እንኳ ጥቁረቱ ቢጠፋ፣
ነበረ እንኳ ማለት ለወሬም አይከፋ።
በክፋም በደጉም ካንተ ያልተለየ፣
አብሮህ የዘለቀ ጣዩን ቁሩን ያየ፤
ሽበቱ ይሻላል ቆርጦ ከተለየ።
አላወቅኸው የኔን የጉዳቴን መጠን፣
ይኸው የራስ ቅሌ ቀርቶብኝ ራቁቱን፤
እመክትበት አጣሁ ጸሀይና ቁሩን።

ያኔ ድሮ ድሮ ሲጀምረው አመል፣
ከጠላቴ መክሮ አብሮ ከቅማል፤
ያሳርሰው ነበር ይህን የራሴን ቅል።
በሙቅ ውሀ አጥቤ ቅባት ቀባብቼ፣
እልገው የነበር ማበጠርያ አንሶቼ፤
ላጭቼውም የነበር ቅማሉን ላጠፋ፣
ሳልጠረጥር ጠጉሬን እንደዚህ ሊከፋ።
ታከቲኩን ቀይሮ በፎሮፎርኛ፣
ያበግነኝ ቀጠለ ከፋቱ ምንኛ።
ኑብስ አወቅሁኝና ነገር ሁሉ ገብቶኝ፣
ሳቆለማምጠው ሳደንቀው ሲያስውበኝ፤
ሰፌድ ቁርጥ ስለው ጆንትራ ሳበጥር፣
አንድ አይኔን ስጨፍን በአፍሮ ከለላ ስር፤
ኮረዳዎች ለጉድ ይከንፉልኝ ነበር።
አንተው በሄድክበት በመሀል ፒያሳ፣
ደግሞም በአራት ኪሎ ታቹን መካኒሳ፣
እኔም ሳልሄድ አልቀር ተዘነጋኝሳ።
በሲኒማ ኢትዮጵያ በአድዋ በአምፒር፣
በኮረዳዎች ታጅቤ ሳልዝናናም አልቀር።
ይኸው እንደ ጠጉሬ እነርሱም ከድተውኝ፣
"ላጤው ጡረተኛ" ለመባል በቃሁኝ።
ያለ እርሱ እንደማልኖር ገምቶ ጠርጥሮ፣
ይጥመለመል ገባ ሳበጥረው አፍሮ።
ለካስ አላረፈም ነበረ ሲያደባ፣
እንደ ወሰለተ የውስጥ አዋቂ ሌባ።
አወይ የኔ ጠጉር መመለጡ የበዛ፣
ዋርካ እሚሆን መስሎት ሾላ ወይም ዋንዛ።
አጀማመሩ ላይ ..................
የምታጠበውን ፊቴን እያሰፋ፣
ቀስት እየመሰለ ከግንባሬ ጠፋ።
ሁዋላም 'M' ን ሰራ ብለው ይነግሩኛል፣
እኔ በመስተዋት 'W' ይታየኛል።
አጨራረሱ ላይ ..................
ቀለም ገባው መሰል ተመህል አናቴ፣
'O'ን ሰርቶ አረፈው ታውቆት ባዶነቴ።



መች ያለምክንያቱ ፈረንጅ አፍ የገባው፣
ቢጠጋ ነው እንጂ አይዞህ ወደሚለው።
በእኔ ያልተገለጠ ምን ጉድ አለ ከቶ፣
ያስቅብኝ ያዘ ጨረቃ አበጅቶ።
ጨረቃና ኮከብ ባናቴ ላይ ሰርቶ፣
ተአረቦች ተማክሮ ነጎደ እኔን ትቶ።

ተያ በሁዋላማ ምኑ ይነገራል፣
ጠጉሬ ሲመለጥ ጆሮዬ ይስቃል።
ጎልቶ መታየቱ ክብር እየመሰለው፣
ሀሩሩና ቁሩ ይውላል ሲያደብነው።
ጥርሴም አላርፍ አለ መገንጠል ከጅሎ፣
መንጋጋዬ ከስር ወጣ ተመንግሎ።
ስንቱን ያሳየችኝ ጨሉሌዋም ዐይኔ፣
ወግ አይቅረኝ ብላ አምጻብኝ በእኔ፤
መሄድ እያቃተኝ በመደናበሬ፣
ሞራ እየለበሰች ትስቃለች በእግሬ።
አንተስ ማስተዋልህ አልከዳህም ከቶ፣
መቆጨትን ያውቃል አእምሮህ አጥርቶ።
የምትነግረው አለህ ለባለ ጠጉሮቹ፣
ለወሬ የማይመች የመላጣዎቹ።
የመገንጠል ነገር በጠጉር አይቆምም፣
ኩላሊት እምቢ ይላል ይለግማል ልብም፤
እግር ይረሳል መሄድ ይሸፍጣል እጅም።
እንግዲህ ካስተዋልክ አቀብ ቁልቁለቱን፣
መሆን ስትችል ያኔ ሳትሆን የቀረውን።
ንገር ለሚሰሙ ጠጉር ላደላቸው፣
መሸበት እንዲሻል ይወቁ አስረዳቸው።
የአንድነትን ውበት የሳምሶንን ታሪክ፣
ባንተ ያምራልና ቀስቅስ ሁሉን ስበክ።
አዋቂ እምንልህ ሽበቶ አስተማሪ፣
ስራ ማፋለጊያ ባይሆንም መስካሪ፤
የእድሜ ኮሌጅ ገብተህ ብታገኝ ነው ዲግሪ።
እንዲያው የኔ ነገር አሳቤም ፍራቴ፣
ተበትኜም ብሞት ኩነኔ መግባቴ።
እንዲሁ አንድ ባንድ በመገንጠል ሴራ፣
ባዶ ሬሳ ሳጥን እንዳይቀብሩ አደራ።
በጠሎት አግዘኝ ወለላዬ ወንድሜ፣
እማጠንሀለሁ ባዶ ራሴን ቆሜ።

ከትንሣዔ
ሠኔ 2008

